**መቻል ታከለ**

# <u>ወደ ሁለት ጎራ ያዘመመው የሶሪያ ውጥረት</u>

በሶሪያ ህዝብና መንግስት የሚገኙበት ሁኔታ ፈጥኖ ለመውጣት ከባድ አዘቅት፡፡ ውስብስብ እንጂ፡፡ የስርዓቱ አራማጆች፣ ህዝቡ ራሱና የአረብ ደጋፊዎቹ እንዲሁም አጎራባቾቹ ቱርክና እስራኤል ብሎም ጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ሌሎች አገራት ዝንባሌ ሲታይ ቀጣይ እርምጃውና ፍጻሜውን መተንበይ ይከብዳል፡፡ ሰልፈኞቹ ወይም አስተዳደሩ የመሸነፍ አዝማሚያ ሳይታይባቸው አቀጣጣዮች በየአቅጣጫው የአቅማቸውን ያህል ወናፎቻቸውን ንፋስ እየሞሉ እያራገቧቸው ይገኛሉ፡፡ እ.ኤ.አ. ማርች 15/2011 ለሬዚዳንት በሽር ጥሩ ቀን አልነበረችም፡፡ በደቡባዊ ትንሽ ከተማ መንግስትን በመቃወማቸው ጉዳት የደረሰባቸውን ተማሪዎችን ጉዳይ በመቃወም የአካባቢው ነዋሪዎች ጎዳና ወጡ ወደ ደማስቆም እንደሰደድ እሳት ተዛመተ፡፡ አስተዳደሩም አልቦዘነ ከበድ ያለ ምላሽ ሰጠ፣ ሰልፉም በአገሪቱ ተቀጣጠለ፡፡ ወደ ኤፕሪል አካባቢ ከ"ቁንጥጫውና እርምጫው" በተጨማሪ ጥቂት የማይባሉ አስርት ዓመታት ያስቆጠረውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መንግስት አነሳ፡፡ ነገሩ በዚህም አልቆመም፡፡ ስለዚህ አሁን ዓለምን ወደ ሁለት ጎራ የከፈለ ያስመሰለው ዓይነት ወደ ኃይል እርምጃ ገቡ፡፡ ታንኮችንና ከባድ መሣሪያዎችን በመላክ ሰልፍ ባለባቸው አካባቢዎች ድብደባ ተያያዙ፡፡ ይኸው እስካሁን አንድም ተሸናፊ ወይም አሸናፊ ወገን ሳይታይ ዓመቱን ዘለለ፡፡

## አሁን ያለው ስርዓት ሁኔታ

እ.ኤ.አ. 2000 ላይ በአባታቸው ሐፌዝ አላሳድ ሞት በእግር የተተኩት የዛሬው የሶሪያ ፕሬዚዳንት በሽር አላሳድ ታላቅ ወንድማቸው ባሲል አላሳድ በመኪና አደጋ ባይሞቱ ኖሮ ለዚህ ላይበቁ ይችሉ እንደነበር ይነገራል፡፡ ከስድስት ዓመታት የመሪነት ልምምድ በኋላ ሶሪያውያን በድጋሚ ድምፃቸውን በመስጠት ለሁለተኛ 7 ዓመታት መርጠዋቸው ነበር፡፡ ሆኖም በሙስና መስፋፋት፣ ከሶሪያ ህዝብ 10 በመቶ ያህል የሆኑት 'አላዋይት' ጎሣዎች የአገዛዝ ዘመን መራዘምና የአብዛኛው የአገሪቱ ሱኒዎች መጨቆን መነሻ ምክንያቶች በአረቡ ዓለም የተቀሰቀሰው አመፅ ገንፍሎ በደማስቆ ወደ አደባባይ ወጥቶ ይኸው ዓመቱ አለፈ፡፡ እሳቸውም በአሸባሪዎች ስም እየተዋጉ አማፂያኑም ሳይቦዝኑ እስከተያዘው ወር ከ10,000 ሺ በላይ ዜጎች እንደሞቱ ይታመናል እንደ ተ.መ.ድ. መረጃ፡፡

ፕሬዚዳንቱ ቁልፍ የአመራር ቦታዎችን በአላዋይት ዘመዶቻቸው እንዲሸፈኑ በማድረጋቸውና፣ የአገሪቱ ገዢ ፓርቲ የሆነው የባኣዝ ፓርቲ ቁንጮ ላይ በመቀመጣቸው ከምዕራቡ ተገልለው በማዕቀብ ቢደቆሱም፣ ወዳጆቻቸው ቢርቋቸው፣ አብላጫ የሱኒ ሙስሊሞች አይንህ ላፈር ቢሏቸው ጆሮ ዳባ ልበስን መርጠዋል፡፡ በጆም ከፋም ዓለምአቀፍ ማህበረሰብ በሶሪያ የ"ሰላም ዞን" ለመፍጠር መንቀሳቀሳቸውን በመቃወም በተቀናበረ ሁኔታ የአላሳድ ደጋፊዎች ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተዋል፡፡ እነኚህ

የአላሳድ ደጋፊዎች የሶሪያ ሰልፈኞች የተቃውሞውን 1ኛ ዓመት በማክበር ላይ በነበሩበት ተቃዋሚ ኃይሎች ላይ ጥቃት መሰንዘራቸውም ማን አለብኝነትን እንደሚያመላክት የኦባማ አስተዳደር ባለስልጣናት ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ የተለየ ስያሜ ሊሰጡት ይችላሉ።

## የስርዓቱ ተጋላጭነት

የአላሳድ መንግስት በተለያዩ የስልጣን እርከኖች የራሱን ሰዎች በመሰየም በአላዋይት ጎሣ የውስጥ ክፍፍል መሰረት ስልጣን በመከፋፋል፣ ሌሎች ጎሣዎች በተለያየ መልኩ በመከፋፈል እንዲሁም አኩራፊ ሱኒዎችን፣ ስጋት ላይ የወደቁትን ክርስቲያኖች ድጋፍ የማግኘት ሙከራ ነው ይላሉ ተንታኞች እስካሁን የአላሳድ አስተዳደር እያደረገ ያለውን ጥረት። ግን በአጭር ጊዜ ባይባልም በረዘመ ጊዜ ስርዓቱን ለውድቀት ሊዳርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች መኖራቸው ይገለፃል።

መጀመሪያው ፕሬዚዳንቱ የሚመኩበት የአላዋይት ካልሊየህና ሙክሽሉፍ በሚባሉ የውስጥ ጎሣዎች ከመኖራቸውና መንግስቱ በተጠቀሱት ሁለቱ ጎሣዎች ላይ መመስረቱ የመንግስት ህዝባዊ መሠረቱን ያጠበዋል ይባላል። እንዲያውም ዓመፁ በተጀመረ ሰሞን የመንግስቱ መመስረቻ የሆኑት እነዚህ የጎሣ አባላት ወደተቃዋሚዎች የማዘንበል አዝማሚያ እንደነበራቸው የመካከለኛው ምስራቅ ተንታኞች ያስረዳሉ። የኋላ ኋላ የመንግስት ፕሮፖጋንዳና ቀውሱ ጎሣዊ መልክ እየያዘ ሲጠናከር ለበርካታ ጊዜ የተቆናጠጡትን ስልጣን አልፎም ህይወታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ በማሰብ ለሥርዓቱ ታማኝነታቸውን መግለጽ የጀመሩት ይላሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ ለፕሬዚዳንቱ ጎሣም ሆነ ቤተሰብ የውስጥ መከፋፈል ሊፈጠር ይችላል በተለይ በቀጣይም ጎሣው የስልጣን ባለመብት እንደሚሆንና የሚመጣው መንግስት ለአላዋይት የጎሣ አባላት ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደማያመጣ ከተማመኑ የሚለው ሌላ መላ ምት ነው። ሆኖም ይህ ብዙም የሚያስኬድ እንዳልሆነ በሊባኖስና ኢራቅ ተጀምሮ የነበረውን የስልጣን መጋራት አለመሳካቱን በመግለጽ ያስቀምጣሉ።

በሱኒም ሆነ በአላዋይት የቢዝነስ ማህበረሰብ ላይ ቀውሱ የፈጠረው የኢኮኖሚ ጉዳት ሌላ የስጋት ምንጭ ተደርጎ ይጠቀሳል። በርካቶች ድርጅቶቻቸውን ለመዝጋት ወይም ለጊዜው ለማቋረጥ በመገደድ ወደ ተስፋ ቢስነት እየገቡ ነው። ተቃውሞአቸውን ወደ አደባባይ ባያወጡም የሱኒ ባህላዊ ነጋዴዎች ለሥርዓቱ ጥልቅ ጥላቻ እንዳላቸው ተፅፏል። የአላሳድን አስተደደር ማን ሊተካ እንደሚችል አለመታወቁና የሚመጣው ከአላሳድ የተሻለ ጥሩ አማራጭ ስለመሆኑ መተማመኛ አጡ እንጂ ጎዳና ለመውጣት ዳድቷቸዋል። በሀገሪቱ እየተስፋፋ የመጣው ድህነት፣ ሥራ አጥነት ለሥርዓቱ አደጋ ነው። በርካታ ሚዲያዎች እንሚያትቱት ስርዓቱ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የኢኮኖሚ ማዕቀብ የውጭ ገቢን በመቀነሱ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲሁም ታማኞቻቸውን ለመደጎም ወዳለመቻሉ እያደረሰው

ነው፡፡ መሪው የመካከለኛ ህብረተሰብ ያቀፈው የበኣዝ ፓርቲ ወኔና የሥርዓቱ መሳሪያ እንዳልነበር ሁሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን እስከዚህ ነጥብ ከተተነተነው መረዳት አያዳግትም፡፡ እስካሁን ለአሳሳድ መንግስት ሽንጣቸውን ገትረው በመዋጋት ቀጥ አድገው የቆሙት ታማኞቹ Republican Guard ልዩ ኃይሎችና የሦስተኛና አራተኛ ብርጌድ አባላት መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ታዲያ ተቃዋሚዎቹ ከነሱ የተሻለ መሳሪያና ስልጠና እያገኙ ከገጠሚቸው ሊደክሙ የሚችሉበት፣ አሁን በዓላማነት የተነገራቸው ሀገሪቱን ከውጭ ወራሪዎች የመከላከልና የጎላን ተራሮችን መልሶ መያዝ ነው፡፡ ሆኖም የሚያደርጉት በተቃራኒ ወንድም ዜጎቻቸውን እየወጉ መሆኑን ሲረዱ በርከት ያለ የሰራዊት ማፈንገጥ እንደሚኖርም ኦክስፎርድ አናላይቲካ ደይሊ ብሪፍ የተባለ ጥናት ማዕከል ይገልጻል፡፡ ከሰሞኑ የተፈጠረው አደጋ ደግሞ ምናልባት የሥርዓቱን መሪዎች የሚያሳስብ ይመስላል:: የአሳሳድ አማች አሴፍ ሻውካት እጅግ የሚፈሩ የሶሪያ የደህንነት ኃላፊና ጄኔራል ዳውድ ራጃህ የመከላከያ ሚኒስትር መገደላቸው ለበሽር አሳሳድ አስተዳደር ከባድ ጉዳት መሆኑን የዓለም ሚዲያዎች ይተነትናሉ፡፡ በፀረ ዘመቻው ከነበራቸው ከፍተኛ ሚና አንፃር ሚቾቹን ማን ይተካቸዋል? እየተባለ፣ ፕሬዚዳንቱ 'ቀኝ እጃቸውን' አጡ የሚሉም አልጠፉ፡፡

## የተቃዋሚዎቹ ፍተሻ

የተቃውሞ እንቅስቃሴው በተጀመረ በሁለት ሳምንቱ መልክ እንዲይዝ የተቃዋሚዎች ጥምረት የሶሪያ ብሔራዊ ም/ቤት ተቋቋመ፡፡ ይህ ቡድኑን በሶሪያ "ከሶሪያ ብሔራዊ ትብብር ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ" (NCB) ጋር የነበረውን ተወዳዳሪነት ያደበዘዘው መስሎ ነበር፡፡ ግን ለጊዜው ነበር፡፡ ሁለቱ አካላት(የተቃዋሚዎች ጥምረት SNC ና NCB) በሦስት መሰረታዊ በሆኑና ተቃዋሚውን በሚከፋፍሉ ጉዳችዮች ይለያያሉ፡፡ ብሔራዊ ም/ቤቱ የውጭ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትና ተቃዋሚን ማስታጠቁን ሲደግፍ ካለው ስርዓት ጋር ምንም አይነት ድርድር ይቃወማል፡፡ ሆኖም በቅርቡ የወጣውን የኮፊ አናንን የሰላም እቅድ ተቀብሏል፡፡

በቅድሚያ (NCB) ከዚህ ፍፁም ተቃራኒ አቋም ይዟል፡፡ የውጭ ኃይል ጣልቃ ገብነትንና ተቃዋሚዎችን ማስታጠቁን ውድቅ በማድረግ ፀረ-ስርዓት ብጥብጡ ቆሞ እንደመርህ ለሚከተለው ድርድር አመቺ መንገድ እንዲከፈት ይፈልጋል፡፡ በዚሁ አቋም ይመስላል ከአሳሳድ ወዳጅ ሩሲያ ጋር ጥሩ ቀረቤታ ያለው፡፡ ያዝልቅላቸው እንጂ መልካም የመገናኛ መንገድ እንዳላቸውና መሪው ሐሰን አብዱልአዚዝ ሞስኮን እስከ መጎብኘትም ደርሰዋል፡፡ ግን በዚሁ ወቅት የፀጥታው ምክር ቤት የአረብ ሊግና ሌሎች የሶሪያ ወዳጆች እንዳሰቡት “ሰብአዊ ጣልቃ ገብነት ሊፈለግ እንደሚችል ፍንጭ ሰጥተዋል፡፡ ሁለተኛው ያለያያቸው ነገር አገር ውስጥ ሳሉና በስደት ላይ በሚገኙ የሶሪያ ተቃዋሚዎች ይታጠቁ ”ኧረ አይሆንም ለአካባቢው ሰላም አስጊ ነው” እሰጣ ገባ አንዱ ነው፡፡ በሀገር ውስጥም እንደ Al-Waltan ጥምረት ያሉት

የNCBን አቋም ይጋራሉ፡፡ አዲስ የተመሰረቱ (የሶሪያን መንግስት መገንባት) አማፂያንን ማስታጠቁን በእጅጉ እየተቃወሙ ለውጭ ጣልቃ ገብነት ጥሪ ያቀርባሉ፡፡ ይህን እውነት ከሶሪያ ብሔራዊ ም/ቤት ያፈነገጡ እንደ የሶሪያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (SPDP) ደጋፊ ናቸው፡፡ የመጨረሻው ልዩነት ብሔራዊ ም/ቤቱ የአመራር ብቃትና ተፅዕኖ ፈጣሪነት ያለው ችግር ነው፡፡ ከወዳጆቻቸው የተሰጡና ቃል የተገቡ ለትግሉ የሚያስፈልጉ ድጋፎችን ለአባለቱ በማድረሱ ውስንነት እንደሚታይ የመካከለኛው ምስራቅ ማዕከል ከፍተኛ አማካሪ የዚድ ሳይድ ይናገራሉ፡፡ ድርጅቱ አካባቢያዊና ዓለምአቀፋዊ እውቅና ከማግኘት ባለፈ የስርዓት ለውጥ ወይም በድርድር የስልጣን ሽግግር ለማድረግ የሚያስችል ተጨባጭ ፖለቲካዊ ስትራቴጂ ማቅረብ አለመቻሉም ይወሳል፡፡

## የተቃዋሚዎች ውጤት አለመፋጠን

በአጠቃላይ ዓመት ባሳለፈ ትግል ለምን አማፂያኑ ድል አልተቀዳጁም ለሚለው ጥያቄ Christian Monitor Science 7 ዋና ዋና ምክንያቶችን ይተነትናል፡፡

የሶሪያ ሰልፈኞች እስካሁን ባደረጉት ትግል የጠሉትን የበሽር አላሳድ ስርዓት ማስወገድ አልቻሉም፡፡ ለዚህም በመንግስት በኩል እየተፈፀመ ያለው አካላዊ ተፅዕኖ ወደግባቸው እንዳይደርሱ እንዳደረገ ይጠቀሳል፡፡ የሞት፣ አሰቃቂ ቅጣትና ያለምንም የህግ መሰረት ዘብጥያ መጣል የተወሰኑ የተቃዋሚ ደጋፊዎችን በቆራጥነትና ቁርጠኝነት መታገሉ ቀርቶ ለመሸበር ይዳርጋል፡፡

ተቃዋሚዎቹ በቁጥር እየበዙና ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ መልዕክት ለማስተላለፍ በሚያስችላቸው ውጤታማ መልኩ እንዴት መደራጀት እንዳለባቸው የተማሩ ይመስላሉ፡፡ ሆኖም ባለብዙ አቅጣጫ ጥራቱ በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ ምንም እንኳን በርካታ ተከታዮችን በተለይ ከተፅዕኖ ፈጣሪ የሱኒ ንግድ ማህበረሰብ በማፍራት እውነተኛ አንድነት ኖሮ የብዙዎቹን ልብ ትርታ መንካት ቢችሉም አላሳድን ከሥልጣን ሊፈነቅል የሚችል ያህል ጠንካራ አይደሉም፡፡

ከጅማሮው አንስቶ ተቀዋሚዎች ሰላማዊ ተቃውሞ ሲያሰሙ መቆየታቸው እሙን ነው፡፡ ግን እስከ መቼ ሰልፈኞቹ 'በሰላማዊ ተቃውሞ' ታክቲክ ይቀጥላሉ የሚለው እያጠያየቀ መሆኑ አልቀረም፡፡ መንግስት በሰራዊቱ እያራገፋቸው ከመሆኑና ያገባናል ባይ የሀገር ጥቅም ወይም ሐይማኖታዊ ተቆርቋሪነት ያላቸው ወገኖች ገብተው ዓላማቸውን ሊያስቱ ይችላሉ፡፡ በግልፅ የሌላ ኃይል ሊደግፍ ከገባ የአላሳድ የውጭ ደጋፊዎችም ዝም ብለው አያዩምና የውጭ ሰርጎ ገብ ውጤቱም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ሌላው ችግር ከእስላማዊ ወንድማማቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲን በእስልምና አክራሪነት ከመመልከት የመነጨ ምናልባት ተቃዋሚዎች ድል ቢቀናቸው በአካባቢው "ከድጡ ወደ ማጡ" እንዳይሆን የተሰጋ ይመስላል፡፡ ለዚህም ምዕራቡ ዓለም ካለው መንግስትና ከተቃዋሚዎች (የሙስሊም ወንድማማቾች) ለመምረጥ ግራ የተጋባ ይመስላል፡፡ ከዚህ ያልተናነሰ ግምት የተሰጠው መንስኤ ከስርዓቱ ጋር የሚደረገው ድርድር ነው፡፡ ከስርዓቱ ጋር የሚደረገው ውይይትና ድርድር ለዴሞክራሲ ስርዓት የሚደረገውን ግስጋሴ ይገታል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ አሁን አሁን ግን ተቃዋሚዎቹ በመጠኑ የተደራጁና ወዳጆቻቸውን ያስፈነጠዘ የበሽር አላሳድን ወገኖች ደግሞ በቁጭት ከንፈር ያስነከሰ ድል እየቀናቸው ነው፡፡ አማቻቸውን ጨምሮ አራት ቱባ ባለስልጣናትን በፍንዳታ በመግደል የፕሬዚዳንቱን አንጀት አሳርረዋል፡፡ በተለያዩ የውጊያ ግንባሮች ድል እየተቀዳጁ ስለመሆኑም አንዳንድ የመካከለኛው ምስራቅ ተንታኞች ይገልፃሉ፡፡ እነኚህን በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ክፍተት ፈጥረዋል የተባለለትን ግድያ ማን ፈፀመው? ግቢው በኃይለኛው የሚጠበቅ የመከላከያ ግቢ ሆኖ ሳለ እንዴት የተቃዋሚ ኃይሎች ገብተው መሀል ህንፃው ላይ ቦምብ በማፈንዳት ጥፋት አደረሱ? የሚለው እያጠያየቀ ይገኛል፡፡ ታዲያ ናዲም ሻሐዲ ከለንደን ቻታም የምርምር ተቋም የአላሳድ ሥርዓት በራሱ የተዋሃደ አይደለም ያሉት እውነት አይመስልም? የስርዓቱ አራማጆችን ያስተሳሰራቸው በዙሪያቸው ያለው አሉታዊ ውጥረት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የአላሳድ ደጋፊዎች በአጠገባቸው ያለውን ያምናሉ ምክንያቱም በውስጣቸው ጥርሱን ያገጠጠ ጭንቀት አለና፡፡ ግን ሁሉም ነገር እነሱ እንዳሰቡት የሚታመን አይመስልም፡፡ ማማ ላይ ወጥተው ዙሪያውን የሚጠብቁት ታማኞች ጭምር ከጥርጣሬ ገብተዋል፡፡ እንደውም ለንደን የተባበሩት መንግስታት ኃይል አንድ ወር ጊዜ ብቻ እንደሚበቃው መግለጿ ተቃዋሚዎቹ መጠናከራቸውንና የአላሳድ አስተዳደር እድሜው እያጠረ መምጣቱን ልብ ማለት ይገባል አንዳንድ ባሙያዎች፡፡

## የዓለምአቀፍ ማህበረሰብ ግንዛቤ

በሶሪያ ውስጥ ከሚካሄደው የእርስ በርስ እልቂት ባሻገር በርካታ የሚባሉ አካባቢያዎችና ዓለምአቀፋዊ አመለካከቶች ይስተዋላሉ፡፡ ሩሲያና ቻይና የፀጥታ ም/ቤትን የውጭ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት በሶሪያ ይቃወማሉ፡፡ ጣልቃ መግባቱን የሚደግፉት ተስማምተውና ማረፊያ ከጎረቤት ቱርክ አግኝተዋል፡፡ በኔቶ አማካይነት መሳሪያ ወደ ቱርክ፣ ደቡባዊ የሶሪያ ወሰን ማንቀሳቀስም ጀምረዋል፡፡ ከአውሮፓ ህብረት ማዕቀፍ ጋር በተያያዘ የእንግሊዝ ኢንሹራንስ ድርጅት ከባድ መሳሪያ ጫኝ ተብላ ለተጠራጠረችው የሩሲያ መርከብ መድህን አልሰጥም ማለቱ በየአቅጣጫ ለመጎንተል የሚደረገውን ጥረት ያመላክታል፡፡

በተመሳሳይ ቱርክ ከሰሜን ጦር ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ጋር ለመተባበር በምትዘጋጅበት በአሁኑ ወቅት የራሷ የሆነ የተጋላጭነት አደጋ ስላለባት ይመስላል፡፡ ቱርክ የሱኒ ደጋፊ የሚለውን ካርድ

የምትጫወተው ለሁለት ነገሮች ነው፡፡ አንድም በጣም ለሚያሰጋት የኩርድ አማፂያን አሁን በሶሪያ ካለው መንግስት ጋር ጥሩ ግንኙነት ስላለው ወስኗን ተሻግሮ ለመግባት ይቀለዋል የሚል ጥርጣሬ ስለጠነሰሰች ይመስላል፡፡ ከዚህ ተጋላጭነት በተጨማሪ በሶሪያ እየታየ እንዳለው የሱኒና የሌላ ሃይማኖት ክፍፍል ወደ ቱርክ ቢገባ የሱኒና አላቪ መከፋፈል አገሪቱን ሊሰነጥቅ የሚችል ከፍተኛ አደጋ በመሆኑ የሶሪያ መንግስት ተወግዶ የዚህ ዓይነቱ ወሬ እንዲጠፋ ከማሰብ የመነጨ ነው ይላሉ ሐሊል ካራቬሊ የተባሉ የማዕከላዊ እስያ ካውከስስ አጥኚ፡፡ ቱርክ ለወትሮው የሶሪያ ረጅም ወሰን የምትጋራና ውስብስብ ዓይነት ግንኙነት የነበራት አገር ናት፡፡ በፈረንጆቹ 1990ዎቹ የኩርዶች የሠራተኞች ፓርቲ (PKK) በአብደላ ኦቻላ እየተመራ ቱርክን የፈተናት በሶሪያ ድጋፍ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህ ታሪክ ሆኖ ተቀብሯል ባይባልም ሀገሮቹ ለመትነን የተቃረበ ግንኙነታቸውን አድሰዋል፡፡ በተለይ ከአውሮፓውያን 2006 ወዲህ የነበራቸው ኢኮኖሚያዊ ትስስር እየተሻሻለ መጥቶ ቱርክ በሶሪያ ያላት በንግድና ኢንቨስትመንት በዓመት 20 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ እንደነበር ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ታዲያ ቱርክ አሁን የምታራምደውን ዓይነት አቋም ለምን ያዘች ለሚለው የሀገሪቱ አንዳንድ ምንጮች እንዲሁም አሌክስ ጃክሰን የተባሉ የፖለቲካ አደጋዎች ተንታኝ የተወሰኑ ነጥቦች ያስቀምጣሉ፡፡

ቱርክ በቅርቡ በሶማሊያ ጉዳይ የሚካሄደውን ስብሰባ በማስተናገድ ያላትን ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ከፍ ለማድረግ የምታደርገውን ጥረት ያመለክታል፡፡ በዚህ ሩጫዋ ወቅት እርሷ ሰፊ ድንበር የምትጋራ እያለች በሶሪያ ጉዳይ ሌላ አካል እንዲቀድማት እንደማትፈልግ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ ሁለተኛው ምክንያት በመካከለኛው ምሥራቅ ያላት ፍላጎት እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ የመካከለኛውን ምሥራቅ ትስስር በአዲስ መልኩ በመፍጠር ባለቤት ሆና ለማገልገል ምኞት እንዳላት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ መግለጻቸው ይታወሳል፡፡ በክልሉ ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆን ያለመች ሀገር አቅሟን ለማሳየት አጋጣሚውን እየተጠቀመች መሆኑም በመላ ምቶቹ ተካቷል፡፡ ከእነዚህ መንስኤዎች ሌላ እንዲሁም አሳማኝ የሚመስለው ከሳዑዲ አረቢያ፣ ኳታር፣ ዮርዳኖስ ከመሳሰሉት ሀገራት የሚጋሩት ክልሉን የሱኒዎች ክልል (The Sunni Arc) የማድረግ ህልም ነው፡፡ ቱርክ ከዜጎቿ ከ70 በመቶ በላይ ሱኒ ሙስሊሞች እንዳሏት ይታወቃልና፡፡ አጋሮቿን ደጀን አድርጋ የሶሪያ ተቃዋሚዎችን እየደገፈች ናት፡፡ በተቃራኒው ያሉትን ሩሲያ፣ ቻይና እና ኢራን ለጊዜው ብንተውም መሪው የቱርክ ፍትህና ልማት ፓርቲ (AKP) ከሀገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ በተለይ (15%) የአለቪና የኩርድ ተቃዋሚዎች መሪው ፓርቲ በሀገር ውስጥ ያለውን ጭቆናና ልዩነት ሳይፈታ በሌላ ሀገር ጉዳይ መግባት ተገቢ አይደለም በማለት ድምፃቸውን እያሰሙ ነው፡፡ ቱርክ ግን ማንም ምንም ይበል፣ ትክክል ትሁን አትሁን፣ የውጭ ፖሊሲዋ "ከጎረቤት ጋር ምንም ዓይነት ችግር አለመፍጠር" (Zero Problems with Neighbours) የሚል ቢሆንም ገፍታበታለች፡፡ ይህ ቱርክ ለሶሪያ ሱኒ አማፂያን የምታደርገው ድጋፍ በአገሪቱ ሱኒዎችንይበል ሲያሰኝ የአለቪ ማህበረሰብ አካላትን እና ኩርዶችን ግን አስከፍቷል፤ በግልፅም የሚተቹ አልጠፉም፡፡ ጦርነት ያልበቃት ይመስል የቱርክን የጦር አውሮፕላን መትታ በመጣሏ "የእጇን

ታገኛለች" ፋከራው ተበራክቷል። በሁለት የተከፈለው የኃያላኑ የጥቅም ግጭት አካባቢውን አሁን ካለበት በበለጠ ሊያተራምሱት እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም።

ለነገሩ ሁላቸውም በሰላማዊ ህዝብ ወገንተኝነት፣ ዴሞክራሲን በማስፈን፣ የአካባቢ ፀጥታና በመሳሰሉት ስም የሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት እውን ከልብ የመነጨ ነው? እንዳሰቡትስ የጠሉትን ሥርዓት አንስተው ህዝቡ የተጠማውን፣ እነሱ ያለሙት ዓይነት ዲሞክራሲ ተገኘ? እኔ አይመስለኝም። በኢራቅ ሳዳም ሁሴን ከቀበሮ ጉድጓድ አውጥተው ለገመድ፣ ከባዓቦ ይልቅ የጋዳፊ ይሻላል። የግብፁ ሆስኒ ሙባረክ ከወንበራቸው ተንሸራተው ለወህኒና ራስ ለመሳት በቅተዋል፣ ኮሎኔል ጋዳፊም ለመግለፅ በሚያሳቅቅ መልኩ ወደማይቀርበት ተሸኝተዋል። የቱኒዚያ የህዝብ አመፅ ሳይበረታ፣ የየመኑ መሪም በፍንዳታ እስከመቃጠል ደርሰው ሾልከዋል። ሁሉም በአንድ ወይ በሌላ መልኩ ህዝቦቻቸውን ጎድተዋል፣ ከዜጎቻቸውም ተቃውሞ ገጥሟቸዋል፣ ምናልባት የኢራቁን እርግጠኛ ባልሆንም የዓለምአቀፍ ማህበረሰብ በተለይም የምዕራቡ ዓለም ጣልቃ ገብቶም ሳይገባም እነዚህ ሰዎች ተወግደው ከሞላ ጎደል መንግስታቸውም ፈርሷል። ሆኖም እንደታሰበው ህዝቦቻቸው የናፈቁት ሰላም ሰፍኖ ዲሞክራሲ በምትካቸው ተመሰረተ ለማለት ግን አያስደፍርም። ሲሆን ሲሆን ተግባብቶና ተደማምጦ የራስን ችግር በራስ ለመፍ□ት መጣጣር ነው እንጂ በውጭ ኃይሎች ሰላምና ዴሞክራሲን ለማግኘት ማለም ከቅዥት ይሻላል

ሁሉም ሀገር ከየራሱ ጥቅም አንፃር የሚሯሯጥባት በተለይ ፈርጣማ ጡንቻ ያላቸው አገሮች እንደ ሩሲያ ዓይነቱ የሚኖራቸው ሚና በቀላሉ አይታይም። በሀገሪቱ በተፈጠረው ትርምስ ኃያላኑም ሀገሮች ለሁለት ተከፍለዋል። አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ልክ እንደ ጋዳፊ የሶሪያ መሪ ተወግደው የስርዓቱ ፍፃሜ ይሁን ባይ ናቸው። ሩሲያና ቻይና ደግሞ እንዴት ሲደረግ የውጭ ጣልቃ ገብነት ይላሉ። "የባሰ አለና አገርህን አትልቀቅ" እንዲባል እኒሁ ሁለቱ የምዕራቡ ዓለም በጥርጣሬ ከሚመለከታቸው ኢራንና ሶሪያ ጋር 90,000 የሚደርስ በከባድ መሳሪያዎች የታገዘ ጦር ከቀጣይ የፈረንጆች ወር ጀምሮ ለማሰልጠን እንዳሰቡ ሚዲያዎች ያራግባሉ። እንደ ዴይሊ ቴሌግራፍ ዘገባ የሩሲያዋ መርከብ Mi25 በቅፅል ስም "በራሪ ታንኮች" የተሰኙ ከባድ የጦር መሳሪያዎችን ለአላሳድ መንግስት እያስተላለፈ እንደሆነ ተጠቅሷል። ይህ እውነት ሆኖ የሶሪያው ሰውዬ ይበልጥ የሰለጠነ (ወይም ለአገሩ ህዝብ የሰየጠነ) ሰራዊት ካገኙ በሀገሪቱ ያለው ጉዳይ መቋጫው ምን ይሆን? ጊዜ ይፍታው።

እንደው በተመረጡ ሀገሮች ጣልቃ ስለመግባት ስናነሳ አንዴ እየተደፈጠጠ ሌላ ጊዜ እየተዜመ ስላለው የዊስትፋሊያ ሉዓላዊነት መርህ ማንሳት ተገቢ ይሆናል። ሐሳቡ እ.ኤ.አ. 1648 በአውሮፓ ታላላቅ አገሮች የአገራት ድንበርና በውስጥ ጉዳይ የውጭ ኃይል ጣልቃ አለመግባት የሚያቅፍ የሰላም ሐሳብ ነው። የዓለምአቀፍ ግንኙነት ቲዮሪስቶች እንደሚሉት የዌስትፋሊያው የሰላም ሀሳብ ዘመናዊ ግንኙነት

ለመፍጠር ጠቃሚ መሆኑን ያትታሉ። በውስጡም የሀገራት የሉዓላዊነትና መሠረታዊ በራስ የፖለቲካ ውሳኔ መብት፣ በሀገራት መካከል ህጋዊ እኩልነትና በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርሆዎች መሆኑን ይገልፃሉ። ግን አካራካሪ መሆኑ አልቀረም። በተለይ ከግሎባላዜሽን ፅንሰ ሀሳብ ጋር ሲታይ ሉዓላዊነት የዓለም አገራት አንዱ በአንዱ የሚወሰን ነው። ለሰብዓዊ፣ በዴሞክራሲ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሽብርተኝነትን በመከላከሉ አንድ ሀገር በሌላው የአገር ውስጥ ጣልቃ ሊገባ ይችላልና የዌስትፋሊያ የሰላም ሐሳብ የቀድሞ ትርጉም ከአሁኑ ወቅት ጋር አብሮ አይሄድም ይላሉ ፊል ዊልያምስ የተባሉ ፀሀፊ። ግን ምን ይሆን? በኮትዲቯር፣ በሊቢያ ለአማፂያን ከምዕራቡ ዓለም አሰጥቶ በየመን አልፎ በሶሪያ የተለሳለሰ ይመስላል። በሶሪያ ምንም እንኳን መንግስት በሰልፈኞቹ ላይ ማስፈራሪያ ተኩስና አፋኝ ጭስ እየተጠቀመ ሳይሆን እስከ ታንክ ያሉ አረር አዘሎችን ነው። "ያወጣ ያውጣ " በሚል በሊቢያ ጋዳፊና ደጋፊዎቻቸው መሽሻ እስኪያጡ አብዮተኞችን በመደገፍ የተሯሯጡ ምዕራባውያን ለአላሳድ ጊዜ የ'ዌስትፍሊያ ሰላምን ጠቅሰው ይሆን አስራ አራት ወራት ወደ ከ10 በላይ ህይወት ሲቀጠፍ ወደ ማዕቀብና ድርድር ያዘነበሉት? ነው ብሎ አፍ ሞልቶ መናገሩ ይከብድ ይሆናል የሶሪያው። ምናልባትም በሊቢያ ያን ያህል ለፍተው አሁን ያለው ሁኔታ በሌላ ሀገር ጣልቃ ከመግባት በፊት ቆም ብሎ ማሰብን አስተምሯቸውም ይሆናል። ወደ ተቃውሞ መነሻ የቀድሞ የሶሪያ ቅኝ ገዢዋ ፈረንሳይ ከመንግስት ጎን ስለነበረች የኃያላኑ ሐሳብ ሚዛን አልደፋም ነበር። በወቅቱ የአረቡ ዓለምም ዝምታ ውጦት በተለይ ቱርክ ከአላሳድ ጎን መሰየሟ፣ ቀጣዩን ማየት ይከብዳል። ጣልቃ መግባታ ሲፈለግ እንደ ቦሲኒያ ኸርዞጎቪኒያ የምዕራቡ ዓለም ቀኝ እጅ ኔቶ ሆነ ሩሲያ ባይግባቡም ሊፋጠጡ ይችሉ ነበር። እንደሶሪያ በሁለት ተከፋለው የእጅ አዙር ፍልሚያ ከማድረግ ይልቅ።

## የእጅ አዙር ውጊያ

የሶሪያ ትርምስ ከመንግስትና ህዝብ ግጭትነት እየዘለለ መጥቷል። በሐይማኖት መመሳሰል አሊያም ከብሔራዊ ጥቅም በመነሳት የአካባቢና ዓለምአቀፍ ማህረሰብ በሁለት ተከፍሎ የስርዓቱን አራማጆችና ተቃዋሚዎችን አለሁልህ! እያለ ይገኛል። ግጭቱን እንደ ሺኣና ሱኒ ግጭት የወሰዱ የአካባቢው አገሮች እንደየአቋማቸው በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተቃዋሚዎችንና መንግስትን እየደገፉ ነው። በአንድ ወገን በባህሬን ጉዳይ በቀጥታ ያገባኛል ብላ ሰራዊቷን ያስፈረሰችው፣ የምንጊዜም የሱኒ የበላይነት ማረጋገጥ የምትፈልገዋ ሳዑዲ አረቢያና ቱርክ የአላሳድን ተቃዋሚዎች "አይዟችሁ በርቱ" በማለት ድጋፋቸውን እያስተላለፉ ነው። እንደ መሣሪያ የሚጠቀሙበትን ሳዑዲ የምትመራው የአረብ ሊግ እንዲሁም ቱርክ ለውጭ ኃይል በድንበር አካባቢ እንዲሰፍርና አብዮተኞችን እንዲረዳ መፍቀዷ መሆኑን ሚዲያዎች ይገልጻሉ። ሌላው ቀርቶ የበላይነትን ፖለቲካና የሎጂስቲክ ድጋፍ ያገኝ የነበረው ሓማስ ውለታ ከወገን አይበልጥም ብሎ ይመስላል አማፂያንን በመርዳት ጽ/ቤቱን ከደማስቆ በመቀየር የሶሪያ መንግስት በሱኒ ዜጎች ላይ የሚያደርሰውን ደም ማፍሰስ ተቃውሟል። ሺኣው ሂዝቦላህ (ከሊባኖስ) በተቃራኒው የአላሳድ

መንግስት አቋም ማድነቁን ቀጥሏል። ሳዑዲ አረቢያ በአካባቢው ከቱርክ ጋር ለሶሪያ ብሔራዊ ም/ቤት እውቅና በመስጠት፣ ለአማፂያኑ ወታደራዊ ድጋፍ፣ የ’Nofly Zone’ በማቋቋም የሶሪያ ስደተኞችንና ነፃ የሶሪያ ሰራዊት (FSA) ለመከላከል የሰሜን ጦር ቃልኪዳን ድርጅት (NATO) የሱኒ መንግስትን በማፅናት የበላይነትን ለመቆናጠጥ ኢራን ደግሞ ሶሪያን ጨምሮ ከፐርሽያ ባህረሰላጤ እስከ ሜዲትራኒያን የሺኣ የበላይነት እንዲረጋገጥ እንደሚሻኮቱ ግልፅ ነው። በሶሪያ ያለው ፍጭትም የዚህ ነፀብራቅ ይመስላል።

ከዚህ ባሻገር በዓለምአቀፍ መድረክ ብሄራዊ ም/ቤቱ(SNC) እውቅና አግኝቶ የሽግግር መንግስት መመስረት እንዲችል ጥረት ያደርጋሉ። በተለይ ከመጀመሪያው ጎረቤቶች የአረብ ኃይሎች የሶሪያ ተቃዋሚዎችን በማስታጠቅና የፋይናንስ ድጋፍ በማፍሰስ ደማስቆ እየወቀሰቻቸው ትገኛለች። ሊባኖስ፣ ዮርዳኖስ፣ ኢራቅ እንዲሁም ሳዑዲ አረቢያ በቱርክ ለመቆጣጠር በሚያዳግት የሶሪያ ድንበር በኩል ለሰልፈኞች እየረዱ መሆኑ ይነገራል። የኳታርም ጎልቶ አይታይ እንጂ የምዕራቡን ዓለም አቋም እንደምትደግፍና እንደምታራምድ ነው መረጃዎች የሚያሳዩት። ለዚህም ነው የመንግስት ሰራዊት አሊፖና ደማስቆ ትልልቅ ስትራቴጂያዊ ከተሞች እንዲሁም ሆምስ ለተባለች የሊባኖስ ድንበር ከተማ አተኩሮ የሚዋጋው። ኢድሊብ ደግሞ በሰሜን ምዕራብ አካባቢም ወሳኝ ቦታ ነው። ምክንያቱም ነፃ የሶሪያ ሠራዊት (FSA) መሠረት በመሆኑና ለቱርክ አዋሳኝ በመሆኑ የአላሳድ ኃይሎች ለአፍታም ቸል አይሉትም።

ነገር ግን ከሱኒና ሺአ የአባባቢው ሽኩቻ ባሻገር በአውሮፓውያን ጁላይ መጨረሻ ጄኔቫ ላይ በሶሪያ ጉዳይ በተካሄደው ምክክር ቱርክና አሜሪካ የደረሱበት ድምዳሜ ትኩረት ስቧል። ሰላማዊ የመንግስት ሽግግር በማድረግ ሰላማዊት ሶሪያን የማስቀጠሉ ተስፋ መሟጠጡን ሁለቱም ገልፀዋል። በመሆኑም ለሶሪያ አማፂያን ወታደራዊ ትብብር በማድረግ ግፊት ለመፍጠር መስማማታቸው ጭምር ተነግሯል። እንዴት የሚለው ግልፅ ባይሆንም በስብሰባው የነበሩት ሩሲያና ቻይና ብሎም ያልነበረችው ኢራን ተመጣጣኝ እርዳታ ለአላሳድ እንደሚያደርጉ አያጠራጥርም። አንዳንድ ምልክቶች እንደሚያሳዩት ፀረ-ምዕራብ አቋም አራማጆች የሆኑ እስላማዊ ሰርጎ ገቦች በ"ሶሪያ ነፃ ሠራዊት" ውስጥ መኖራቸው እሙን ነው። ህልማቸው እስላማዊት ሪፐብሊክ ሶሪያ ተመስርታ ማየት በመሆኑ የማይፈነቅሉት ድንጋይ ስለማይኖር ቀውሱን በቀላሉ መገመት አያዳግትም። አሁንም ሌላ ስጋት አልታጣም። በሶሪያ ጉዳይ እስራኤል በወታደራዊ ጣልቃ መግባቱ ከተካተተች ጉዳዩ ሌላ መልክ ሊይዝ ይችላል ይለናል ዴይሊ ኒውስ ከቱርክ። ቴላቪብ ጣልቃ ከገባች በክልሉ በሽር አላሳድ ያጡትን መሠረታዊ ድጋፎች መልሰው ሊያገኙ ይችላሉ። አሊያ ግን ይላሉ የፖለቲካ ተንታኞች የሱኒ መንግስት በክልሉ የማቋቋም ህልማቸው ወደ ቅዥት ተቀይሮ ለኢራን ፈንጠዝያ እንደሚፈጥሩ ያውቃሉና። ጠንክረው እየሰሩበት ነው። ያከሆነ ደግሞ በመካከለኛው ምስራቅ በብዛት የከተሙት አማፂያኖኞቹ ሺአዎች ይነግሱና በሁለቱ ዋልታዎች ሱኒና ሺአዎች መካከል የማይወጣ ሁከት ይገባል ይላሉ አሎን ቤን-ሜደር የተባሉ ተንታኝ።

በተለይ የመንግስት ታማኝ ወታደሮች የአላዋይት ጎሣ አባላት በምዕራብ የአገሪቱ ክፍል ህዝቡ ላይ ፍርሃት ለማሳደር እየሰሩ ያሉት ግፍ እንደክርስቲያኖቹ ያሉትን አነስተኛ ወገኖች እያራደ መሆኑ የዘርፍ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። አኳኋናቸው ከ15 ዓመታት በፊት በቦሲኒያ ተከስቶ የነበረውን የዘር ማጥፋት የወንጀል አካሄድ ዘዴ እየተጠቀሙ ስለመሆኑ መቀመጫቸውን ሊባኖስ ያደረጉት ፖለቲከኖች ያስረዳሉ። እንደ ተንታኞቹና በተለይ የተ.መ.ድ. ግምት መሰረት ቢያንስ 10,000 ያህል ከተቃዋሚዎቹ (ሱኒዎች) እንዲሁም ወደ 2,600 ከአላሳድ ደጋፊዎች ለህልፈት ተዳርገዋል። ችግሩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው ደግሞ ተቃዋሚዎቹ ሴቶችንና ህፃናት የጉዳት ሰለባ ማድረጋቸው ነው። በተለያዩ የሶሪያ ከተሞች የደረሰው እልቂት በምሳሌነት ይጠቀሳል።

## ምን ይከተል ይሆን?

የአባታቸውን "ገድል" ደገሙ የሚባልላቸው የአላሳድ መንግስት በጥንካሬም በተጋላጭነትም ይገለጻል። እንደባለሙያዎቹ የኦክስፎርድ ትንተና ማዕከል ለአራት አስርት ዓመታት ያህል አገሪቱን ሲገዛ በፖለቲካ ተቋማት ባኣዝ ፓርቲን ጨምሮ ያለው መሰረቱ የላላ ነው። ይልቁንስ ጥልቅ ባልሆነ በአላዋይት፣ በሰራዊት፣ ደህንነት አገልግሎትና በንግድ ተጠቃሚ የሆኑ ጥቂት ሲኒዎች ድጋፍ የኖረ ነው ይባላል። ስለሆነም በአጭር ጊዜ ባይሆንም ተጠቃሚዎች ደጋፊዎቹ ጥቅማቸው እንዳይነካ ማመን ሲጀምሩና ክፍፍል ሲፈጠር በድርድር መልኩ ሽርተት እንደሚል ይናገራሉ። የመካከለኛ ምስራቅ ተንታኝ ቮልከር ፐርዘስ ቁልፍ በሩስያ እጅ ነው ባይ ናቸው። ምሶሶው ለ"ሰውዬው" ጫወታው አብቅቷልና በድርድር እሳቸውም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው ለፍርድ እንደማይቀርቡና ምንም ጉዳት እንደማያገኛቸው ሲገልጽላቸው ጉዳዩ ያበቃል። ፕሬዚዳንቱ ሩሲያ ቀስ አድርጋ እንዳገለለቻቸው ተረድተው መላ ይሹ ነበር የሚል አቋም አላቸው።

ካልሆነ ግን ለአላሳድ ቤተሰብ ዜጎችን መግደል አዲስ አይደለም። አባትየው ሔፊዝ አላሳድ እ.ኤ.አ. 1982፣ ፌብራሪ ሱኒዎች በሚበዙበት ሓማ በተባለ አካባቢ የተነሳባቸውን ተቃውሞ በታንኮችና ከባድ አራሮች ለ27 ቀናት በመደብደብ ፀጥ ረጭ አድርገዋል። ቀጣዩቹን 18 ዓመታትም ሶሪያን መርተዋል። ታዲያ የዛሬው ፕሬዚዳንት በሽር አላሳድ የዚያኔም በ17 ዓመት ዕድሜ በስርዓታቸው ላይ የተነሱትን ተቃዋሚዎች ሲያንበረክኩ ከ10 እስከ 30 ሺህ የሚገመቱ ሰዎች ተገድለው ሚስተር ሐፌዝም ያለ ምንም ጠያቂ በ69 ዓመታቸው በልብ ህመም በሽታ መሞታቸውን ያውቃሉ። በዚህ ላይ ቻይና በዲፕሎማሲ፣ ሩሲያ በመሳሪያ አቅርቦትና ድጋፍ፣ ኢራን በወታደራዊና ፀጥታ ማማከርና ቬንዙዌላ ነዳጅ በገፍ በማቅረብ ልባቸውን እያደነደኑት ነው። እንዴት በቀላሉ እጅ ይሰጣሉ ይላል ፑንተርስ online የተሰኘ ድረ-ገፅ ትንተና።

እንዲያውም ቤተ-መንግስት የመቆየታቸው ዕድል የካቲት ላይ 42 ከነበረው ወደ 68 በመቶ አሳድጎታል፡፡ ሌሎች ድረ-ገጾች መጠኑን ያሳንሱት እንጂ በቀጣዩ የአውሮፓውያን ዓመት የመቆየታቸው ዕድል ከ50 በመቶ እንደሚያልፍ ያመለክታሉ፡፡ ምናልባትም አሜሪካ በተካሄደው የቡድን 8 አገራት ውይይት ወቅት የተነሳውም ሐሳቡን ያጎላል፡፡ አሜሪካ የሩሲያውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዲሚትሪ ሜድቬዴቭ በሶሪያ ያለው ደም መፋሰስ እንዲቆም አላሳድ ስልጣን ቢለቁ የሚል ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡ የሶሪያ መንግስት ሊወደድም ላይወደድም ይችላል ሆኖም ማንም የማይክደው ጥያቄ ግን በሽር አላሳድ ቢወገዱ የሚተካቸው ማነው? የሚል ነበር የሩሲያ መልስ፡፡ ይኸው ይመስላል አሜሪካ፣ አውሮፓ ወይም አረብ አገሮችን ያሰጋቸው፡፡ እስካሁን መረር ያለ እርምጃ በጋራ ወይም በተናጠል እንዳይወስዱ ያደረጋቸው፡፡ ከዚህ አኳያ በሶሪያ ምድር ካለው የጂኦ ፖለቲካዊ አሠላለፍ እንዲሁም ከዓለምአቀፍ ማህበረሰብ የተለያየ አቋም አንፃር ብሎም ከሶሪያ ወታደራዊና የፖለቲካ አቋምና የተቃዋሚዎች ጥንካሬ አንፃር የሶሪያን መፃኢ ሁኔታ ለመተንበይ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ሁላችንም በየቀኑ በየሰዓቱ የምንከታተለው ይሆናል፡፡

የሶሪያ መንግስት ባዮሎጂካልና ኬሚካል መሣሪያችን በገፍ ቢጠቀምና ፍፃሜው ውድቀት ቢሆን መሣሪያዎቹ በማን እጅ ይገቡ ይሆን የሚለው አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲያውም የሶሪያ አማፂያን ጦርነቱን እየገፉ ያሉት ብቻቸውን አይደለም፡፡ ፀረ ምዕራባውያን አቋም ይዘው የ'እስላማዊ ሪፐብሊክ ሶሪያ' መንግስት እንዲቋቋም የሚል አክራሪ ወገኖች በሰርጎ ገብነት መኖራቸውን የአላሳድ መግስትም ሆነ ሌሎች ይገልፃሉ፡፡ ይህ ከሆነ አላሳድ ሊጠቀሙበት ያሰቡት ባዮሎጂካልና ኬሚካል መሣሪያም ሆነ ለተቃዋሚዎች አንድ ሁለት እያለ የሚደርሰው መሣሪያ የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ ምንም ሆነ ምነ ማን እጅ እየገባ ነው የሚለው የአካባቢው ጥያቄ ነው፡፡ በአካባቢው የሚርመሰመሱት ሐማስ፣ ሂዝቦላህ እንዲሁም አልቃይዳ መቼም አይረሱምና፡፡ ሌላው የሶሪያ ቀውስ ለእስራኤል ደህንነት የሚያሰጋ ከሆነ እስራኤል ጣልቃ መግባቷ አይቀርም የሚል ነው፡፡ ያ ሆነ ማለት ደግሞ በሶሪያ ያለው የኃይል ሚዛን በጠቅላላ ያዛባዋል፡፡ ምክንያቱም አሁን ፕሬዚዳንት በሽር አላሳድን በመቃወም አማፂያንን የሚደግፉት የአረብ አገሮች ያለጥርጥር ሀሳባቸውን ይለውጣሉ፡፡ ሌላውም እንደዚያው ይሆንና ለማሰብ ወደሚከብድ ውጥረት ይለወጥ ይሆን? ፕሬዚዳንት በሽር አላሳድ ይህንን ሁሉ ተመልክተው ይወርዱ ይሆን ወይስ ውጊያውን ቀጥለው እድሜያቸውን ያራዝሙ ይሆን? ቢሆን ግልግል፣ እፎይ ነበር፡፡ መሆኑ አለመሆኑ እንዲሁ አከራካሪ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሶሪያ ልሳነ ምድር ካለው የጂኦፖለቲካዊ አሰላለፍ እንዲሁም ከዓለምአቀፍ ማህበረሰብ የተለያዩ አቋም ብሎም ከሀገሪቱ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና

የተቃዋሚዎች ጥንካሬና ድክመት አንፃር የሶሪያን መፃኢ ሁኔታ ለመተንበይ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ሁላችንም በየቀኑና በየሰዓቱ የምንከታተለው ይሆናል፡፡ ሠላም!

***ፀሐፊው በlibisho@gmail.com ይገኛል!***